# ኢዜማ በሲያትል አማራዎችን ከሰልፍ አፈናቀለ

*(ጋሻው ቀለሙ)*

ዘመን እየተለወጠ በሄደ ቁጥር የአማራዉ ሕዝብ ያለበት ችግር ይቀንሳል፤ ያልተረዳቸዉና በትግራይ ሰይጣኖች የሃሰት ወሬ የተመረዙ ሁሉ ወደ እዉነቱና ወደ ትክክለኛ አእምሯቸው ይመለሳሉ ስንል የባሰዉን እያደር ነገሩ እየተበላሸ ጠላት ከግራም ከቀኝም በአማራ ላይ እየበዛ እየሄደ ከዚህ ደርሰናል። የትግሬ ወያኔዎቹ አማራን የሌለዉን ጸባይ አለው ብለው ስሙን ሲያጠፉ ስለኖሩ አሁን ኢትዮጵያ ዉስጥ ሁሉም ባይሆኑ በዛ ያሉት ብሄርተኞች አማራ የሚለዉን ቃል ብቻ የልጆቻቸዉ ማስፈራርያ አድርገዉታል። ለዚህ የትግሬ ወያኔዎቹን በቅድምያ እያመስገን የእነርሱ ትምህርት ተቀባዮችን የአሁኖችን ኦሮሞዎች ደግሞ ከወያኔዎቹ ተቀብለው የሚሰሩትን እየተመለከትን ነው። አማራው በገዛ እርስቱ በጎጃም መተከል እየታረደ ስጋዉ እየተበላ ነዉ፡ በወለጋ፤ በጉራፈርዳ፤ በአሩሲ፤ በሃረር ወዘተ.... እየተሰቀለ፤እየተቃጠለ፤እየተገደለ ነዉ። ይህንን አልሰማሁም ወይም አላየሁም የሚል ኢትዮጵያዊ ካለ ላለፉት 30 አመታት ኮማ ዉስጥ የነበረ ወይም ከሌላ ፕላኔት የመጣ መሆን አለበት። ይህን ካልኩ በኋላ ካለሁበት ሩቅ ሀገር ስላሳዘነኝ የሲያትል ዋሽንግተን ሰላማዊ ለማለት የሚከብድ ሰልፍ ትንሽ ልበል። እኔ እስካሁን የስልፉ አላማ ምን እንደሆን ሌላው የተረዳው አልመሰለኝም። ለምን ቢባል ሰልፉ ኢትዮጵያን አስከብረን አማራን አዋርደን ቤታችን እንገባለን ተብሎ የተወጣ ሰልፍ እንደነበር ምንም ጥርጥር አልነበረዉም። ያ ካልሆነ አማራ ታረደ ቢባል የሚከፋው ከአራጁ በቀር ማን ሊሆን ይችላል? ወገኖቻችን የጅምላ ጭፍጨፋ ተፈጽሞባቸዋልና መቆም አለበት ቢባል ሰው በመሆኑ ብቻ ይህን የሚቃወም እንዴት ሊኖር ይችላል? ይህንንስ የሚቃወሙት ሰው መርጠው ባያደርጉት ሌሎቹ ሲያደርጉት ይህን መፈክር ይዛችሁ ለሞቱት አትጭሁላቸው ብለው ማለታቸው አሁንም በሚቾቹ ከሚደሰት በቀር ሌላ ማን ሊኖር ይችላል? በሰልፉ ተዋናኝ የነበሩት የዘመኑ አጎብዳጆችና ለመጣዉ ሁሉ እራሳቸዉን አሳልፈው የሚሸጡ የበዙበት እንደነበር በስራቸው ተጋልጧል። ለምን ይህን አልክ የሚለኝ ካለ ማብራራት እችላለሁ። እኔ ከደረሰኝና ከሰበሰብኩት ቀጥተኛ ምስክርነት የሚከተለዉን ማቀነባበር ችያለሁ። ሰልፉ ላይ የነበሩት ሁለት ቡድኖች ሲሆኑ። 1ኛው ከአማራዉ ራስ የማይወርደው የድሮው ግንቦት 7 የአሁኑ ኢዜማ አቀንቃኞች ሲሆኑ 2ኛው ደግሞ  የአማራ ወገኖቻቸው ሰቆቃ፤ በየቦታው መታረድና መገደል እንዲቆም የአለም ሕዝብ እንዲያዉቅላቸዉ መፈክር ይዘው የወጡ የአማራ ሕዝብ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። ከዚህ ላይ አንድ እንዲታወቅ የሚያስፈልገው ነገር ከሁለተኛዉ ቡድን ዉስጥ ከተሰለፉት መካከል የአማራዉን በየቦታዉ መጨፍጨፍ የሚቃወሙ አማራ ያልሆኑ ህሊና ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ጭምር በሰልፉ እንደተሳተፉ ነው። ይህ ባለበት ሁኔታ ነው አንድ ወጣት የአማራን ጭፍጨፋ አወገዝክ ተብሎ በግንቦት7/ኢዜማ ጀሌዎች በተጠሩ ፖሊሶች እንዲደበደብ የተደረገው። ለምን? ብለን እንድጠይቅ እየተገደድን ስለተጎዳው ወጣት በኋላ ልመለስና እነዚህ ሰዎች ከአማራው ጋር ያላቸው ጠብ ምንድን ነው የሚለዉን እንመልከት። ትንሽ ወደ ኋላ እንሂድና እስኪ አመጣጣቸዉን እንየው፤በፊት የግንቦት 7 አሁን ደግሞ የኢዜማ መሪ ነኝ የሚለው የአራዳ ጩለሌ ከነታምራት ላይኔ ጋር ተለጥፎ የአዲስ አበባ ታዋቂ መምህራንን ከስራቸው አፈናቅሎ እርሱ ሄዶ ገብቶ ዩኒቨርሲቲዉንም ሐገሪቱንም ከወያኔዎቹ ጋር አጨማልቆ ነገሩ ጠበቅ ሲል የተጣላ መስሎ ቅንጅትን እንዲያፈርስ ስራ ተሰጥቶት ይህንን ከፈጸመ በኋላ ወደ አሜሪካ ሄዶ ታጋይ ነኝ አለ። ቀጥሎ ከሌላው ጠላፊ የወያኔ ቅጥረኛና የዉጭ ሰላይ ጋር ተዳምሮ ግንቦት 7 የሚል ድርጅት አቋቋምን አሉና አማራን ሊያጠፉ ተሰማሩ። በዉጭ ያለው አማራ ለወገኑ እንዳይደርስ የሚያደናብር መልእክት (*አዎ ማደናገርን ለኦሮሞዎቹ ያስተማሩ እነርሱ ናቸው*) እያስተላለፉ የዉስጥ ስራቸዉን ኢሳት ብለው ቲቪ ከፍተው አማራዉን ማለብ ቀጠሉ። (*አንባብያን አማሮች ቂሎች ስለሆናችሁ ነው ትሉ ይሆናል፤ አዎ እኔም ያን ለማለት ፈልጌ ነው*) ሲያንስም ደግሞ ከዋናው የአማራ ጠላት ከግብጽ ድጎማው ኪሳቸዉን ሞላውና ድራማው

እስኪያቆም ድረስ ቀጠለ። ከዚያ እንኳን ወያኔን ሊፈጁ የፈጁት ቢኖር ኤርትራ የነበሩትን የአማራ ተዋጊዎች ነበር። ብቻ ይህ እራሱን የቻለ አርእስት ስለሆነ በሌላ ጊዜ በሰፊዉ ይዳሰሳል። ቀጥለዉም የአርበኞች ግንባር ታጋዮችን ኢትዮጵያ ሲገቡ ከኦሮሞዎቹ ጋር ተነጋግረው ትጥቅ ፈትተው እንዲገቡ ያስደረጉ እነዚሁ የግንቦት 7/ኢዜማ የአማራ ጠላቶች ነበሩ። ያንን ከነትጥቁ ሰተት ብሎ ገብቶ ባንክ ሲዘርፍ የነበረዉን ኦነግን ሲቃዎሙም አልሰማንም፤ አላየንምም። ይባስ ብለው የጀርመን መንግስት ለአርበኞች ግንባር መቋቋሚያ የሰጠዉን ገንዘብ የኢዜማው መሪና ጓደኛው ቅርጥም አድርገው በልተዋል። ነገር ግን ለማያዉቅሽ ታጠኝ ሆነና ነገሩ ግንቦት 7 ቀለም ተቀብታ ኢዜማ ተብላ አዲስ አበባ ብቅ ካለች በኋላ ኢሳትንም የህዝብ ነው ብለው ማወናበዱን ትተው የግለሰብ አድርገዉት ቁጭ ሲሉ በሚሊዮን እያዋጣ ኢሳትን ከዚህ ያደረሰው አማራ ባዶ እጁን አጨብጭቦ ሲቀር አማራ የአያቴን የጦጃ ማሰርያ የነበረዉን ፊንፊኔን ቀምቶኛልና አማራ ይዉደም ብሎ ተረት ተረቱን መጽሃፍ ብሎ ደርቶብን አማራ ይጥፉ ብሎ ያለን አንድ የግንቦት 7 አመራር ኢሳትን ተረክቦ ቁጭ አለ። ዋናው የኢዜማዉ ዶክተርም ከኦፒዲኦ ጋር ተግባባሁ ብሎ እስክንድር ይሰቀል ሲል፤ ቡራዩ ሲታረድ አላየሁም፤ አማራዎች ሲፈናቀሉ፤ አላየሁም፤ ሲሞቱ ምስክር አምጡ ሲል፤ ማን ይስማው ኦሮሞዎቹ እንኳን ለኢዜማው አብሯቸው በወያኔ እንደ እነርሱ ተጠፍጥፎ ለተፈጠረው ለመንትያ ወንድማቸው ለብአዴንም አልሆኑት፤ ወይ ፍንክች። የኢዜማው ዶር አሁን እየተንጓለለ ይዞት የቀረ አቋም ካለው ያው ተነስቶ እስኪመክት ድረስ መከረኛዉን አማራ እኔም አብሬ አጠፋዋለሁ ነጥብ ያዙልኝ ከሚል ደጅ መጥኛ አድርጎታል ነው ነገሩ፤ ተግባባን? ስለዚህ ይህ አሁን ሲያትል ሰልፍ ላይ የተፈጸመው ከዚህ በፊት ቶሮንቶ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተፈጽሟል፡ ዲሲ ላይም ተፈጽሟል ፈጻሚዎችም የታዎቁ ናቸዉ ለማለት ነው። ለኢዜማ እስክንድር ይፈታ፤ አማራ ለምን ይገደላል፤ የሚል መፈክር መታየቱ ከስራ ስለሚያስወጣቸው አይፈልጉትም። እኔ በበኩሌ የኢዜማ መሪዎች ችግር ይገባኛል ሁሉን ሞክረው አልቻሉም አሁን የቀርቻቸው አንዲት የስራ እድል ብቻ ነው እርሷም የቤተመንግስት በር ከፋችና ዘጊ መሆን ነው፤ በድሮ ጊዜ ስም ነበረው አዎ አጋፋሪ፤ የኢዜማው ዶር ጥሩ አጋፋሪ ይወጣዋል። የኢዜማን አመራሮች ይቅናቸው በስንት አማራ ደም ነግደውና አፊዘው፤ አሹፈው፤ ተሳልቀው ያገኙትን የኦሮሞ አስተዳደር ቤተመንግስት ዋና አጋፋሪነትን ያጽድቅላቸው። ስንት አማራ አስገድለህና አፊዘህ ከዚህ መድረስ በጣም የሚያስቀና ትልቅ እድገት ነው። አንድ መረሳት የሌለበት ነገር ቢኖር ግን አማራ አረብ አይደለም፤ ኢትዮጵያም ሊቢያ፤ ሶርያ ወይም ሶማሊያ አይደለችም። አማራው እስካለ ድረስ ደግሞ እንደነዚህ ሐገሮች አትሆንም። ምክኒያቱም ለአማራው ከኢትዮጵያ ሌላ ሐገር የለዉም (አልፋ ወኦሜጋ)። ነገሩ ሁሉ ከልኩ ሳያልፍ ግን አማራን ከተኛበት መቀስቀስ የገሃነምን በር መክፈት እንዳይሆን እፈራልሁ። አማራ እንዲጠፋ መመኘት ኢትዮጵያ እንድትጠፋ መመኘት ነው። ወደድንም ጠላንም ሃቁ ይህ ነው። ኢትዮጵያ ከጠፋች ደግሞ አማራን የምትጠሉ ሁሉ አብራችሁ ነው የምትጠፉት። የሰርቅነዉን ይዘን ከቀጣሪ ፈረንጆች እና አረቦች ሐገር እንኖራለን ብላችሁ ከማሰባችሁ በፊት የተከዜ ዋሻዎችን ሄዳችሁ እዩና በማን አስከሬን እንደተሞሉ ስትመለከቱ ይገባችኋል። አይ ካላችሁ ደግሞ አማራው ላይመለስ ቀስቅሳችሁታልና ለጀብዳችሁ መልካም እድል እላችኋለሁ፤ ሞክሩት። ኢዜማዎች እየተላላኩ ለምን በአማራ ላይ ጥላቻ እንደሚፈጥሩ ጠቅለል ባለ መልኩ ላቀርብ ሞክሬአለሁ።

የአማራ ወገናችሁ በደል ተሰምቷችሁ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ልትሆኗቸው ሰልፍ ለወጣችሁ ኢትዮጵያውያን ምስጋናየ ከፍ ያለ ነው። በአማራ ሆነ በወላይታ ሆነ በጋምቤላ ወዘተ.. የሚፈጸም ግፍ ሌላ ስም የለዉም ግፍ፤ ግፍ ነው፤ መጮህ ካለብን እንጮሃለን። ያም ብቻ አይደለም ከወገኖቻችን ጋር እራሳቸዉን ለማይከላከሉ ለመከላከል ዝግጁ መሆንም አለብን። ሲያትል ላይ ወጥታችሁ ለወገኖቻችሁ በታገላችሁ ወያኔ ናቸው (very old trick) እያሉ ስማችሁን ሊያጠፉ ቢሞክሩ አይግረማችሁ ይህን እናንተን ለማሸማቀቅ ከወያኔ የተማሩት ታክቲክ ነው። እነዚህን ነገ ታሪክ ይፋረዳቸዋል። በዚህ ሁሉ ግርግር ደግሞ ከኢዜማ ሰዎች አንዱ ወጥቶ እኔ ጎንደሬ ነኝ እያለ ሲፎክር ይታያል። ምን ማለቱ እንደሆነ እራሱም የተረዳ ስለአልመሰለኝ ትንሽ ልምከረው፤ ጎንደሬነት ጣኦት አይደለም ጎንደር ብዙ አርበኛ

ጀግኖች እንዳሏት ሁሉ ጥቂት ባንዳ ከሃዲም አይጠፏትም። ለምን ቢባል ጎንደር ያሉት እንደሌላው አካባቢ ሁሉ እግዚአብሄር የፈጠራቸውው ሰዎች እንጅ ከሌሎች የተለዩ መንፈሶች አይደሉም። ይህን ካልኩ በኋላ በሌላ በኩል ደግሞ ጎንደሬነት 17 አመት ሲንፏቀቅ ኑሮ የገባዉን ወያኔ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ጠራርገው አባረው ከትግራይ ዋሻ ወስደው የሚሸጉጡ ጀግኖች ደግሞ አሏት። እነርሱ ግን ጎንደሬ ነን እዩን እዩን ብለው አልፎከሩም። ስለዚህ ቀዝቀዝ በል ጎንደሬነት እንደዚህ አይደለም። ጎንደሬነት በስራ ነው የሚታየው ግን፤ ግን አልሰሜን ግባ በለው ነዉና ነገሩ ጥቂት አንዳንድ ነገሮች ለዚህ ጎንደሬ ነኝ ለሚለው የኢዜማ ደጋፊ ልጠቁመው እወዳለሁ።

በረከት ስምኦን ጎንደሬ ነው ከቴዎድሮስ አድሃኖም ጋር ከ 5 ሚሊዮን በላይ አማራዎችን አስፈጅቷል። አሉላ ሶሎሞን የጎንደርን እህል እየበላ ያደገ ትግሬን አይቶ የማያዉቅ ጎንደሬ ነው ትግራይ ሚዲያ ሀዉስ ብሎ ከፍቶ ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ አማራን ለሚያጠፉ ሰይጣን ሲሰግድ ይዉላል። አበባ ተፈሪ የሚሏት ጎንደሬ ከናንተ ከተማ የምትኖር ናት ይባላል አማራ መጥፋት አለበት እያለች የምትሰብክ ለዘመዶቿም የማታስብ እብድ ናት። ጎቤ መልኬን ያስገደለው ወይም የገደለው በትግሬ የተገዛ የዘመዱ ልጅ ጎንደሬ ነው፤የአርማጭሆ ጀግኖች ያለቁት በሚከፈላቸው ጠቋሚ የአካባቢው ሰዎች ነው፤ የበለሳዉን ፋኖ አረጋን ሊያስገድል በወያኔ ያስከበበው ከየት የመጣ ይመስልሃል? አስቻለው ደሴን ያስገደለውስ ማነው? የጉናዎቹ ፋኖዎችስ እንዴት አለቁ? ያ ሁሉ የጎንደር ጀግና ለየብቻ ሲለቀም የነበረው በወያኔ ጥንካሬ ነው ብሎ የሚያምን ካለ በምኒልክ ጊዜ የደነቆረ መሆን አለበት። አማርኛ የሚናገሩት ብአዴኖች ናቸው በገዛ ወገኑ ጎንደሬዉን በጎንደሬው፤ ሸዋዉን በሸዋ፤ ወሎዉን፤ ጎጃሙን፤ ባጠቃላይ አማራዉን በአማራዉ ያስጠቁት። ወያኔ በምን አቅሟ ነው ያን ጀግና ህዝብ ልታጠቃው የምትችል? ጎንደሬ ነኝ ወዳለው ወንድሜ ልመለስና ለኢዜማ በማገልገልህ ከላይ ከጠቀስኳቸው ሰዎች የምትለይበት በምኑ ነዉ? እስኪ ከቤትህ ሂድና በመስታዉቱ ውስጥ የምታየዉን ያንተን ምስል በደንብ አስተዉልና ከነማን ጋር ዉየ መጣሁ ብለህ ጠይቅ፤ ያኔ ማንነትክን ታገኘዋለህ። "ጓደኛህን ንገረኝና ማንነትህን እንግርሃለሁ" ነው እኮ ነገሩ። እባክህ ወገኔ ሁሉንም ብነግርህ ጊዜዉም ቀለሙና ወረቀቱም አይበቃኝም፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሆድ ባዶ ይቀራል ይላል የአገሬ ሰው። እኔ የምልህ ተመከር የወገኖችህን በደል ለይተህ እወቅ ብቻ ነው። ተግባባን?

በመጨረሻ ሳላነሳው የማላልፈዉና በእኔ በኩል ትልቁ አርበኛ ነው የምለው የአማራ ወገኖቹን በደል ይዞ ድምፅ ሲያሰማ በፖሊስ ተይዞ ለተንገላታው ልጅ ነው። እንደሰማሁት ከሆነ ልጁ ከዚህ ተወልዶ ያደገ ነው ስለተባለ እኛን የሚተካ ስለደረሰልን ለግዚአብሄር ምስጋና ይገባዋል። ቀጥሎም በጀግንነቱና በዚህ እድሜዉ ባሳየው አርአያነቱ በእኔ በኩል ባርኔጣየን አንስቸ ጎንበስ ብያለሁ። በግራና በቀኝ ደረቱ የአጼ ቴዎድሮስንና የአጼ ምኒልክን ሜዳል መሸለም የሚገባዉ ወጣት ነው። በዚህ ለከስካሳ ዘመን እንዲህ ያለ ከዚህ ተወልዶ ያደገ ወጣት ለወገኖቻችን ሲቆም ማየትን የመሰለ የሚያስደስት ነገር የለም። ስለዚህ ልጃችን እደግልን፤ አይዞህ በርታ ለወኖችህ ተከራከር፤ አደናቃፊዎችን አትስማ፤ እዉነትን ብቻ ስትከተል ሁላችንም ከጎንህ እንቆማለን። Go young man Go!

*ጋሻው ቀለሙ*
*gashakelemu@yahoo.com*

At last I want to give everyone a good advice,
If you want to be a horse, be a wild horse. Don't let any one ride you.